# የኢትዮጵያ ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ እና የአፍራሽ ኃይሎች ጩኸት!

ከፋኖወዲ ሰመራ

fanowedy@gmail.com

የሰው ልጅ መገኛ፣ የጥንታዊ ስልጣኔ ባሌበት እና ወደ 80 የሚጠጉ የየራሳቸው ታሪክ፣ ባህል፣ ቋንቋ እና የአኗኗር ዘይቤ ያሏቸው ብሔሮችና እና ብሔረሰቦች ያሏት ኢትዮጵያ አምባገንኑን የደርግ ስርዓት በማስወገድ በአዲስ ፌዴራላዊ ዴሞክራያዊ ስርዓት መጓዝ ከጀመረች እነሆ 26 ዓመታትን ተጉዛለች፡፡ በእነዚያ 26 ዓመታት በአጠቃላይ ከሕገ መንግስቱ መፅደቅ በኋላ ደግሞ በተለይ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት ተጎናፅፈዋል፣ እኩልነታቸውንም ሕገ መንግሰታዊ ዋስትና አግኝቷል፡፡ ፆታ፣ ሃይማት ወይም የእምነት፣ ቋንቋ፣ ቀለም ወይም ማሕበራዊ መሰረት ያደረገ ልዩነትም ሕገወጥ እንደሆነ በሕገ መንግስቱ በይፋ ታውጇል፡፡

የመገናኛ ብዙሃን እና የመረጃ ነፃነት እውን በማድረግም ማንኛውም ሰው የመሰለውን ሐሳብ የመያዝም ሆነ የመግለፅ መብቱና ነፃነቱ ሕገ መንግስታዊ ጥበቃ ተደርጎለታል፡፡ በዚህም በርካታ የሕትመት እና የብሮድካቲንግ የሚዲያ ተቋማት የራሳቸው ውስጣዊ ወይም ኤዲቶሪያል ነፃነት በጠበቀ መልኩ እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ፡፡ በእርግጥ እዚህ ላይ በሀገራችን የሚዲያ ኢንዱስትሪ ውስጥ አንድ መሰረታዊ ችግር እንዳለ አይካድም፡፡ በህዝብ ወይም በመንገስት ሚዲያ እና በአብዛኛው የግል በተለይ ደግሞ በግል የሕትመት ሚዲያው መካካል ሰፊ የአሰላለፍ ልዩነት አለ፡፡ የህዝብ እና የመንግስት ሚዲያው የሀገሪቱን ልማት እና ዕድገት በማስተዋወቅ እና በየደረጃው የሚደረጉ ማናቸውም ልማታዊ እንቅስቃሴዎች በማሰራጨት ረገድ የተሻለ ጥረት በማድረግ ላይ የተሻለ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ በእርግጥ በሀገሪቱ የሚመዘገቡ ስኬቶች በተሟላ ሁኔታ ከመዘገብ እና ከማስዋወቅ አንጻርም ከጅምር የዘለለ አይደለም እላለሁ፡፡ ምክንያቱ ይህ ሀገር በራሱ አስተሳሰብ እና የፖሊሲ አማራጭ በጣም የሚያስገርሙ ስኬቶች የሚመዘገብበት እና በአጭር ጊዜ ውስጥ ከአስከፊ ድህነት ተላቅቆ እጅግ ተስፋ ሰጪ የሆኑ ውጤቶች የተገኙበት በዚህም ለሌላ በድህነት ለሚማቅቁ ልማትና ዕድገት ለተጠሙ ህዝቦችም አርአያ የሚሆን መንገድ የሚከተል ሆኖ ሳለ ሚዲያው ግን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴው ከመዘገብ ባለፈ ስትራቴጂያዊ ፋይዳው በሚያጎላ መልኩ እየሄደበት አይደለምና፡፡ በሌላም በኩል የህዝብ እና የመንግስት ሚዲያው

ሀገሪቱ በምታከናውናቸው የልማት፣ የሰላም፣ የዴሞክራሲ እና የመልካም አስተዳደር ጥረቶች የሚያጋጥሙ የአፈፃፀም ስህተቶች እና ጥፋቶች በማውጣት በአንድ በኩል በቀጣይ ተመሳሳይ ስሕተት እንዳይፈጠር በሌላ በኩል ደግሞ ጥፋት የፈፀሙ አካላት በስርዓቱ መሰረት ተጠያቂ እንዲሆኑ በማድረግ የሀገራችን የህዳሴ ጉዞ እንዲፋጠን ከማድረግ ይልቅ ስሕተት እና ጥፋት እያየ እንዳላየ መሆንን ይመርጣል፡፡ በዚህ ደግሞ የመንግስትን ብቻ ሳይሆን የራሱንም ተኣኒነት ጭምር ጥያቄ እንዲነሳበት የሚያደርግ አካሄድ ነው የመረጠው፡፡ በዚህ በኩል በቅርቡ የተጀማመሩ አበረታች ስራዎች አጠናክሮ ከቀጠለ ግን ሚዲያው የሚጠበቅበትን ግዴታ በተሟላ ሁኔታ በመወጣት የህዝቡን እርካታ ለማረጋገጥ የተሻለ እድል አለው፡፡

ከዚህ በተቃራኒ ኣብዛኛው የግል የሕትመት ሚዲያው ደግሞ የመንግስትን ስኬት ለማየት እና ለመስማት ፈቃደኛ አይደለም፡፡ የሀገሩን ስኬት መመዝገብ እንደውርደት የሚቆጥር እና ይልቁንም በአፋፃፀም የሚታዩ ጥቃቅን ስሕተቶችን ከሚገባ በላይ በማጋነን ላይ የተጠመደ ነው፡፡ ከዚህ አለፍ ብሎም የፈጠራ ወሬዎችን በማምረት ጭምር ህዝቡ በተለይ ደግሞ ወጣቱን በማደናገር ላይ የተጠመደ የግል ሕትመት ሚዲያ ቀላል አይደለም፡፡ በተለይ በምርጫ 2007ዓ.ም አካባቢ የታዩ በግላጭ አብዮት የመቀስቀስ እና ሕገ መንስታዊ ስርዓቱን የማፍረስ ግልፅ ዘመቻ የግል የሕትመት ሚዲያው ምን ያህል በፅንፈኛው መንገድ እየተጓዘ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ እዚህ ላይ ቁጥራቸው ጥቂት ቢሆንም የሚዲያ የሙያ ስነ-ምግባር በሚፈቅደው ልክ ስኬትንም ውድቀትንም ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ለማቅረብ የሚሞክሩ የግል የሕትመት ውጤቶች እንዳሉ ግን ሳልጠቅስ አላልፍም፡፡

እናም የመንግስት ወይም የህዝብ ሚዲያ በአንድ ጫፍ የግል በተለይ ደግሞ የግል የሕትመት ሚዲያው ደግሞ በሌላኛው ጫፍ በተፃራራኒነት በመቆም ህዝቡ ማግኘት የሚገባውን ትክክለኛ እና ሚዛናዊ መረጃ እንዳያገኝ ከዚያ አለፍ ብሎም በተሳሳተ መረጃ እንዲደናገር በተለይ የግል የሕትመት ሚዲያው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው ማለት ይቻላል፡፡ እነዚህ ማዶ ለማዶ የቆሙ የሚመስሉ የሚዲያው አካላት በምህዳሩ ላይ ማበርከት የሚገባቸው አወንታዊ አስተዋፅኦ የተሟላ እንዳይሆን እደረጉ ቢሆንም ዴሞክራሲው ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ ነው፡፡ እንዲያውም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ገና በለጋ ዕድሜ ላይ የሚገኝ እና አሁን ብዙ ርቀት መጓዝ የሚጠበቅበት ቢሆንም ከዕድሜው በላይ ብዙ

ርቀት በመራመድ በዚች በገር ከልማቱ ያልተናነሰ ስኬት የተገኘበት ስለመሆኑ ግን የሚያከራክር አይደለም፡፡

የመደረጃት መብትና ነፃነት በተመለከተም እንደሁ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሕገ መንግስታዊ ስርዓቱን ባከበረ መልኩ በሕጋዊ መንገድ ለፈለገው ዓላማ መደራጀት እንደሚችል በሕገ መንግስቱ የተደነገገ እና በተግባርም ብዙ ዕድገት እያሳየ ያለ ነው፡፡ ለዘመናት በሀገራችን የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ዜጎች በነፃት የሚደራጁበት እና ሐሳባቸውን በተደራጀ መንገድ ማቅረብ የሚችሉበት ዕድል ስላልነበራቸውም በተለይ በፖለቲካ ፓርቲዎች የታየው የመደራጀት ሁኔታ በጣም ሰፊ ነው፡፡ አንዳንዴ የፓርቲዎቹ ቁጥር እስከ 90 የሚደርሰውም በሀገራችን ያን ያህል ለፓርቲዎች መራራቅ ሰፊ አጀንዳ ስላለ የተፈጠሩ ፓርቲዎች ሳይሆን ለዘመናት ፀንቶ የቆየውን ክልከላ ሲነሳ ሁሉም በየፊናው ለመደራጀት ካለው ፍላጎት የመነጨ ሊሆን እንደምችል የዚህ ፅሑፍ አዘጋጅ ይገነዘባል፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን ከዴሞክራሲው ለጋነት የሚመነጩ መለስተኛ ውስንነቶች እንዳሉ እና የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ስርዓቱ በቀጣይነት መጎልበት ያለበት ቢሆንም እንደ ስርዓት ግን በተሻለ ሁኔታ ወደፊት እየገሰገሰ ያለ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በመሆኑ ላይ ክርክር የሚነሳበት አይደለም፡፡

በእርግጥ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ተመሳሳይ የሆነ ህዝባዊ ኃፊነት ተስምቷቸው የሀገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም በማስጠበቅ እና በሉአላዊነት ላይ የጋራ አስተሳሰብ ፈጥረዋል ማለት አይደለም፡፡ በዚህም አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች የህዝቡን መሰረታዊ ጥቅም እና ፍላጎት እንዲሁም የሀገሪቱ ዘላቂ ህለውና ጭምር ለአደጋ አሳልፈው እስከመስጠት ይደርሳሉ፡፡ ፅንፈኝነት እና ሁከት በመፍጠር እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች የሚነሱ መለስተኛ ግጭቶች ተባብሰው እንዲቀጥሉ ወይም እንዳይረግቡ አልመውም ይሰራሉ፡፡ ፀረ ኢትዮጵ አቋም ካላቸው የውጭ አካላት በመተባበርም በሀገራቸው ላይ ታሪክ የማይሽረው ክህደት እስከመፈፀም አይመለሱም፡፡

በተለይ በውጭ ሀገራት የሚገኙ አንዳንድ የዲያስፖራ አደረጃጀቶች እማ በገዛ ሃገራቸው ጦርነት በማወጅ እና የህዝቡን የተረጋጋ ኑሮ በማደፍረስ ለዘመናት ተከባብረው እና ተቻችለው በኖሩ ህዝቦች መካከል ዘላቂ እና የማይሽር ቁርሾ እንዲፈጠር ያለ የሌለ የፈጠራ ወሬን እያመነጩ ህዝቡን እርስ በራሱ እንዲባላ ሆን ብለው የሚሰሩ ናቸው፡፡ በዚህ ብቻ ሳይታቀቡም ማንኛው እርዳታ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ የመከልከል ዓቅሙና

ብቃቱ ባይኖራቸውም የመከልከል ዓቅም አለው ብለው ለሚያምኑት የውጭ ኃይል እርዳታ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ እና በዚህም የዕለት ምግብ ፈላጊ ዜጋ ጭምር ምንም ዓይነት የእህል እርዳታ እንዳያገኝ ያደናቅፉልኛል የሚሉትን ሁሉ ከማድረግ አይመለሱም፡፡ የዚህ አባባል ትክክለኛነት ለመረዳት ሀገሪቱ በ2008ዓ.ም ገጥሚት የነበረውን አስከፊ ድርቅ ወደ ርሃብ እንዳይቀየር እና በዚያም የዜጎቿን ህይወት እንዳይቀጠፍ ላይ ታች በምትልበት ጊዜ በውጭ ሀገራት ሆነው የሞቀ ኑሮ የሚኖሩት አንዳንድ የዲያስፖራ አደረጃጀቶች እና ግለሰቦች የእህል እርዳታ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ ለማድረግ ከፍተውት የነበረ ዘመቻ ማስታወስ ብቻ ከበቂ በላይ ነው፡፡

ባለፉት ሁለት ዓመታት በሀገሪቱ የተፈጠረው የሰላም መደፍረስ ሁኔታ ለመፍታ የሀገራችን ህዝቦች እና መንግሰት በሚደርጉት ያለሰለሰ ጥረት ላይም እነዚህ በሀገር ውስጥ እና በውጭ የሚገኙ አፍራሽ ኃይሎች የሚያራመዱት አቋምም እንዲሁ ለትዝብት የሚዳርግ ነው፡፡ ሀገሪቱ በወቅታዊነቱ ሊታይ የሚችል እና በይዘትም ጊዝያዊ የሆነ ችግር እንደገጠማት የሚሸፋፈን ጉዳይ እንዳልሆነ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚገነዘበው እውነታ ነው፡፡ እነዚህ ጊዝዊ የሆኑ ችግሮች ፈትቶ የሀገሪቱን ቀጣይ ዕድገት እንዲቀላተፍ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ለማድረግ ከመረባረብ ይልቅ መንግስት ተዳክሟል በሚል ባትሪው ባለቀበት ካልኩሌተር በተሰራ ሒሳብ ችግሩን ወደማባባስ አዘንብለዋል፡፡ በውጭ ያሉት ፅንፈኛ የዲያስፖራ አባላት እና አደረጃቶችም መንግስት አልቆለታል፣ ውድቀቱ ለማፋጠንም ብሔር ላይ ያነጣጠረ የትግል ስልት በመለኮስ ኢትዮጵያውያን እርስ በርሳቸው እንዲባሉ እና አለፍ ብለውም ኢሳት በግላጭ እንዳወጀው በአንድ ብሔር ላይ የዘር ማጥፋት አጀንዳ እስከማቀንቀን ደርሰዋል፡፡

በሀገር ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ደግሞ በአንድ በኩል የፖለቲካ ምህዳሩ ጠቧል የሚል ከዛሬ ምናምን ዓመት ተፅፎ የተሰጣቸው የላኪዎቻቸው ስንኝ እንደያዙ ያዙኝ ልቀቁኝ ይላሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ገዥው ፓርቲ ከማንኛውም በሰላማዊ እና በሕጋዊ መንገድ የሚንቀሳቀስ የፖለቲካ ፓርቲ፣ ሲቪክ ማሕበራት እና ምሁራን ጋር ለመወያየት፣ ለመደራደር እና ለመከራከር እፈልጋለሁ ብሎ ያቀረበውን ጥሪ ተቀብለው በጠረጴዛ ዙሪያ ሆነው ጥንካሬውን ለማጎልበት እና አለ የሚሉትን ድክመት ደግሞ ለማረም አስተዋፅኦ ከማድረግ ይልቅ የተከፈተውን በርና መስኮት ረግጠው በመውጣት ራሳቸውን ከድርድር ሂደቱ ያገላሉ፡፡ ለምን በድርድሩ አትቀጥሉም ተብለው ሲጠየቁ ደግሞ እኛ

ዋነኞቹ ተቃዋሚዎች ስለሆንን ከሌሎች ተቃዋሚዎች ጋር አብረን መቀመጥ አንችልም፤ ኢህአዴግ እኛን እንደ ዋነኛ ተቃዋሚ መቀበል አለበት፣ የሌሎች ፓርቲዎች ፍላጎት ግን እኛ መወከል አለብን ይላሉ፡፡ በሀገሪቱ የፖለቲካ ምህዳር ጠቧል ብሎ ለክስና ለውንጀላ የሚጣደፍ የፖለቲካ ፓርቲ በምን ሒሳብ የሌሎች ፓርቲዎች እኩልነት ለመቀበል እንደሚከብደው እና የሌሎች ፓርቲዎች ፍላጎት እና ጥቅም በእኔ በኩል ይደርሳቸዋል የሚል ከውጫሌ ውል አንቀፅ 17 የተቀዳ የሚመስል የጭቆና ቀመር በመውሰድ እዴት አድርጎ የፖለቲካ ምህዳሩን እንደሚያሰፋ ግን ያስተዛዝባል፡፡

እነዚህ ከውስጥም ከውጭ ያሉ አፍራሽ ኃይሎች ዓላመቸው አንድ እና አንድ ብቻ ነው፡፡ መምጫ መንገዱ እና ተገቢነቱ ምን ይሁን ምን ስልጣን፡፡ የዘር ማጥፋት ዘመቻ በይፋ በማወጅ ብሔር ከብሔር ጋር እያጋጨም ቢሆን ስልጣን፡፡ በአንድ በኩል ሀገሪቱ ዕድገት የቁጥር ጨዋታ ነው፤ ዕድገት የለም፣ ስለሆንም የተደሻለ እድገት የምናመጣ እኛው ስለሆንን ኢህአዴግ ስልጣኑን ይልቀቅ እያሉ ይጮኻሉ፡፡ በሌላ በኩል ግን በልማት ተቋማት ላይ አነጣጥረው እንዲወድሙ ያደርጋሉ፡፡ ልማት የለም ወይም ይተሻለ ልማት እናመታለን የሚል አካል በምን ሒሳብ ነው የልማት ተቋም የሚያወድመው እና ልማት እንዳይከናወን የሚያደናቅፈው፡፡ እነዚህ አካላት በአንድ በኩል ለወጣቱ የስራ ዕድል እንፈጥርልሃለን እያሉ ሲያደናግሩት በሌላ በኩል ደግሞ ለበርካታ ሺዎች የስራ እድል የፈጠሩ የልማት ተቋማት ያወድማሉ፡፡ የስራ ዕድል ለመፍጠር ጥረት የሚያደርግ አካል ታድያ በምን ሒሳብ ነው የስራ ዕድል የፈጠሩ ተቋማትን ለማጥፋት በእሳት የሚጫወተው፡፡ ደግሞስ ለወጣቱ የስራ እድል በመፍጠር የተሻለ ህይወት እንዲኖርህ አደርጋለሁ የሚለው አካል ወጣቱ ወደ ሁከትና ብጥብጥ ገብቶ የራሱን እና የሌሎችን ህይወት እንዲያመሰቃቅል ትእዛዝ መስጠቱን በምን ሒሳብ ነው! ለዚህም ነው የእነዚህ ኣካላት አልፋና ኦሜጋ ስልጣን መያዝ እና በኋላ ከስልጣን እናገኛለን የሚሉትን ጥቅም ማጋበስ እንጂ ለማንም አይደለም፤ ስሌታቸውም ባትሪው ባለቀበት የሒሳብ ማሽን የተሰራ ነው እሚለው፡፡

እነዚህ አካላት ኢትዮጵያ ያጋጠማት ወቅታዊ ፈተና ጊዝያዊ መሆኑ እና የሀገሪቱ መሰረታዊ መገለጫ ግን ብሩህ ተስፋ ያላት ሀገር እንደሆነችም ለመገንዘብም አልፈለጉም፡፡ ይህ እንዳለሆኖ ስርዓቱ ችግር ሲገጥመው በምን ያህል ብቃትና ዲሲፕልን እንደሚወጣውም ከእስካሁን ተሞክሮው ለመገንዘብ አልፈለጉም፡፡ ደሮ ቢታልም ጥሬዋን አይደል ብሂሉስ!

ሌላው ይቅር እና መንግስት እና የኢትዮጵያ ህዝብ በ2008ዓ.ም የገጠሟቸው ከባድ ድርቅ በውስጥ ዓቅሞቻቸው እንዴት እንደተወጡት እና ድርቁን ተክትሎ የተፈጠረውን ሁኔታ እንዴት ማርገብ እንደቻሉ እንኳን መመልከት አይቻላቸውም፡፡ ቀበሮ በሬው እንትትኑን ይጥልልኛል ብላ ሲትከተለው እንደዋለች ሁሉ እነዚህ አካላትም ኢህአዴግን በፖሊሲ ይሁን የተሻለ ሐሳብ በማቅረብ እንደማይገዳደሩት ልቦናቸው ስለሚያውቅ የውጭ ሀገር መንግስታት ወይም በኢትዮጵያ ዕድገት ላይ አወንታዊ አመለካከት የሌላቸው የኒዮ-ሊበራል ተቋማት የኢትዮጵያን መንግስት እንዲያወርዱላቸው በተለያዩ መንገዶች ሲማፀመኑ እየታዘብናቸው ነው፡፡ ይህም ከኢህአዴግ የእስካሁን ጉዞ ብቻ ሳይሆን ከኢጥዮጵያ የረዥም ዘመናት የነፃነት እና አይበገሬነት ታሪክ እንኳን አንዲት ገፅ ለማየት የፈለጉ አይመስሉም፡፡

በሌላም በኩል እነዚህ አካላት ሀገሪቱ አሁን የገጠማትን ጊዝያዊ ፈተና ሁሉም በፈጣን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ አልፈው አሁን በተሻለ የብልፅግና ደረጃ ላይ የሚገኙ በርካታ የምስራቅ ኤዥያ፣ የላቲን አሜሪካ እና እንደነ ቱርክ የመሳሳሉ የመካከለኛው ኤዥያ ሀገራት በተለየዩ ወቅቶች ከገጠሟቸው ተመሳሳይ የሆኑ ቀውሶች ጋር ብዙም ያልተለየ እንደሆነ መስማት አይፈልጉም፡፡ እውነታው ግን በተለይ ቻይና እ.አ.አ ከ1966 እስከ 1976 እና ኮሪያ ደግሞ እ.አ.አ በ1997 የገጠማቸው ፈተናዎች የችግሮቹ ቅርፅ የተለያዩ ቢመስሉም በይዘት ግን ኢትዮጵያ አሁን ከገጠማት ችግር ጋር በእጅጉ ተመሳሳይ መሆናቸውን ነው፡፡

ለማጠቃለል ያህል አሁን በሀገራችን የሚታየው ፈተና ጊዝያዊ እና ከመንግስት እና ከህዝብ ዓቅም በላይ አይደለም፡፡ መንግስት፣ ገዥው ፓርቲ እና መላው የሀገራችን ህዝቦችም አሁን የገጠማቸው ፈተና በድል በመወጣት የሀገሪቱን ህዳሴ እውን ለማድረግ እየተረባረቡ እንደሆነ ሀገር ውስጥ ያለን ሰዎች በውል የምንገነዘበው እውነታ ነው፡፡ እዚህም እዚያም የሚያጋጥሙን ችግሮች እየፈታን፣ እዚህም እዚያም የሚፈጠሩ ስህተቶችንም እያረምን አሁንም በስኬት ጎዳና የመሄዳችን ምስጢርም ስርዓቱ ራሱን በራሱ የማረም ብቃቱ በመሰረቱ ያልጠፉ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ አሁን ደግሞ ባለፉት ዓመታት በገዥው ፓርቲ ወይም በተለያዩ የመንግሰት መዋቅሮች የተፈጠሩ ችግሮችን በዝርዝር በመለየት እና በተለዩት ልክም ወደተግባር በመግባት የሀገራችን ዕድገት ይበልጥ ተጠናክሮ ለማስቀጠል በሚያስችል መገንገድ  እየተጓዝን ስለመሆኑ እኛ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳንሆን

በቅርቡ በሀገሪቱ የተገኙት የአሜሪካና የሩስያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ጉብኝትም የዚህ መሰረታዊ ስኬታችን ውጤት ሰለመሆኑ ለማስረዳት የፖለቲካ ሀሁ እንኳን የሚያስፈልግ አይደለም፡፡ በራሱ ይናገራልና!

የኢትዮጵያ መንግስት ለውጭ ኃይሎች ተንበርክኮ ከህዝብ የተሰጠውን ስልጣን ይለቃል አሊያም የህዝቡ ይሁንታ ወደ ጎን በመተው ወደ ስልጣን መጋራት ይገባል በሚል የተሳሳተ ሒሳብ ለራሳቸው ከሚዛናቸው በላይ ኪሎ በመስጠት በዚህ ስሌት ስልጣን ለማግኘት የሚቋሚጡ አካላት ካሉ ደግሞ ይሄም በኢትዮጵያ ህዝብ ፊት የማይታሰብ ጉዳይ ይመስለኛል፡፡ ታሪካችን አይደለማ! በጩኸት እና በግርግር መንግስት ይወርዳል የሚል አጉል ተስፋ ያላቸው የሀገር ውስጥ ፖለቲከኞች ካሉም ሲጀመር ፖለቲከኞች መሆን የነበረባቸው አይመስለኝም፡፡ ከህዝብ ፍላጎት እና ይሁንታ ውጭ የሚገኝ የፖለቲካ ስልጣን ሕገ መንግስቱ ሕጉ-ወጥ ማድረጉ መገንዘብም ቢያንስ በሰላማዊ እና በሕጋዊ መንገድ ለሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎች የሚጠቅም ጉዳይ ነው፡፡

የሆነ ድምፅ ኩሽ ባለ ቁጥር በሬው እንትትኑን ይጥልልኝ ይሆናል እንዳለችው ቀበሮ ኢህአዴግም በኩሽታው ፈርቶ እና ተደናግሮ ስልጣን ይለቃል ብሎ ማሰብ የዋህ ፖለቲከኝነት ነው፡፡ ፀሐፊው እስከሚገባው ድረስ ኢህአዴግም ሆነ በኢህአዴግ የሚመራው መንግስት ከህዝብ ሌላ ኣዛዥ ናዛዥ የላቸውም፡፡ የበላይ አለቃቸው ህዝብ ነው፡፡ የስልጣን ምንጫቸውም ህዝብ ብቻ ነው፡፡ ህዝብ በምርጫ 1997ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ እንደታየው ድምፁን ሲነፍጋቸው አሜን ብለው ይቀበላሉ፡፡ በምርጫ 2002ዓ.ም እና በምርጫ 200ዓ.ም በሚያስገርም መልኩ ድምፁ ሲሰጣቸው ደግሞ በተመሳሳይ ሁኔታ አሜን ብለው ይቀበላሉ፡፡ የሀገራችን ተቃዋዎች እንደሚሉት የህዝብን ድምፅ ሲያገኙ ዴሞክራሲው ሰፍቷል ሲነፍጋቸው ደግሞ ዴሞክራሲው ጠቧል ወደሚል የጥቅመኝነት ስሌት ውስጥ አይገቡም፡፡ ባህርያቸውም አይፈቅድላቸውምና!

በእርግጥ ባለፉት ጥቂት ዓመታት የተፈጠሩ የመልካም አስተዳደር ጉድለቶች እና የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮች በአፋጣኝ መፍታት እና የህዝቡን እርካታ በቀጣይነት ማሻሻል የገዥው ፓርቲ እና የመንግስት ከባድ የቤት ስራ እንደሆኑ እና ለተግባራዊነቱም በከፍተኛ ቁርጠኝነትና ዲሲፕልን መረባረብ የሚጠይቅ እንደሆነ እሙን ነው፡፡ ህዝቡ እየጠየቀ ያለው ጉዳይም ይህ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብም ኢህአዴግ እና መንግስት ያልፈቱት ወይም ለመፍታ ጊዜ የወሰደባቸው ችግር ተቃዋሚ ወይም ከውጭ ሆኖ

የሚጮኽ ፅንፈኛ ዲያስፖራ ይፈታልኛል የሚል ቅንጣት ታህል እምነት የለውም፡፡ ይህ መንግስት ችግሮቹ ማየት ከጀመረ ያለምንም ጥርጥር እንደሚፈታውም ከፍተኛ የሆነ እምነት አላቸው፡፡ ለራሱ እንኳን ለይምሰልም ቢሆን መስማመት የማይችል እና የራሱን ችግር መፍታት ያልቻለው ተቃዋሚ ወይም ፅነፈኛው ዲያስፖራ የኢትዮጵያን ችግር የመፍታ ሞራልም ሆነ ወኔ እንደሌለው የሀገራችን ህዝቦች ይቅር እና ተቃዋሚውም ቢሆን የሚያውቀው ጉዳይ ነው፡፡